This is a trial edition prior to its formal edition.
We will be very grateful if you would give us your evaluation on its translation level.
Please, send us your opinion to baptism@bjnewlife.org

*(cover)*

# *በዕውኑ ከውሃና ከመንፈስ እንደገና ተወልዳችኋልን?*

<Front wing>

**ይህ በዘመናችን «የውሃንና የመንፈስን ወንጌል» በመጽሃፍ ቅዱስ መሰረት ለመስበክ የተጻፈ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው፡፡**

ብዙዎቻችሁ ከውኃና ከመንፈስ እንደገና የመወለድ ወንጌል ጋር እንደማትተዋወቁ በእርግጠኝነት ለመናገር እችላለሁ፡፡ ስለዚህም በእያንዳንዱ ስብከት፣ በኢየሱስ ጥምቀትና መስቀል ላይ ከፍተኛ ትኩረትን አድርጌኣለሁ፡፡

ጥምቀት ባይኖር ኑሮ፣ የኢየሱስ በመስቀል ላይ መሰቀል ለብዙዎቻችን ትርጉም የለሽ ይሆን ነበር፡፡ በጥምቀቱ ላይ በተደጋጋሚ የማተኩረውም በዚህ የተነሳ ነው፡፡

የኔ አላማ ይህን ለናንተ ግልፅ ማድረግ ነው፡፡ ሁላችሁም በውኃው ወንጌል (በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት) እስክትባረኩ ድረስም፣ ብደጋግምላችሁ እወዳለሁ፡፡

ከኃጢያት ለመዳን ሁላችሁም በእርሱ የመጠመቅና የደም ወንጌል ወደማመን እንደምትመጡ በተስፋ እጠብቃለሁ፡፡ እንደገና ከውኃና ከመንፈስ ትወለዱ ዘንድም ይህ መጽሐፍ እንደሚመራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

(back cover)

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያለው መልዕክት በውስጤ ያለውን ኃጢያት ሁሉ ለጥቦታል፡፡

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ፕሮፌሰር እንደመሆኔ፣ የዚህን መፅሐፍ የእርማትና የቅጅ ስራ ለመስራት እድለኛ ነበርኩ፡፡ በዚያን ወቅትም ስለ መፅሐፉ ምንም እውቀት አልነበረኝም፡፡ በእርግጥም «የእግዚአብሔር ስራ ነው»፣ በእርግጥም ይህ በህይወቴ ትልቅ ለውጥ ያመጣና ለእምነቴም መሰረትን የጣለ ነበር፡፡

«የድነት ምስጢሩ» የተገለጠልኝም ይህን መፅሐፍ እያነበብኩ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ ይህን መፅሐፍ ከማንበቤ በፊት ወደ ገሃነም የምገባ ኃጢያተኛ መሆኔን አምን ነበር፣ አንብቤ ስጨርስ ግን የድነትን ቁልፍ የያዝኩና ከኃጢያትም የፀዳሁ ሆንኩኝ! እንደገና ተወለድኩኝ፣ እንደገና በኢየሱስ ጥምቀትና በስቅለቱ ተወለድኩኝ፡፡ ይህም በግልፅ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ተፅፎአል፡፡

በጣም ቀላል ቢሆንም ብዙ ክርስትያኖች ግን «እንደገና የመወለድን» ትርጉም ስተውታል! ማድረግ የሚገባው ብቸኛ ው ነገር ማመን ብቻ ነው፣ በዚህም ትድናላችሁ፡፡

-እሌኒ ዳዊ-

# በዕውኑ
# በውኃውና በመንፈሱ
# እንደገና ተወልዳችኋልን?

## የመጀመሪያው እትም

ፓውል ሲ. ጆንግ

# መጀመሪያ ይቅርታ ስለሚደረግላቸው ኃጢያቶቻችን ማወቅ አለብን

**«ማርቆስ 7፡8-9»**

**«የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሳችሁ፣ ጽዋን ማድጋንም እንደማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ። ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ። እንዲህም አላቸው፡- ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። »**

**«ማርቆስ 7፡20-23»**

**«እርሱም አለ፡- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው። ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል።»**

በመጀመሪያ፣ ኃጢያት ምን እንደሆነ ለመግለጽ እወዳለሁ። በእግዚአብሔርና በሰው የተዘረዘሩ ኃጢያቶች አሉ። ኃጢያት ወይም «ሃማርቲያ» በጥንታዊ ግሪክ ቃል፣ ማለት «መሳሳት» ማለት ነው። በሌላ አገላለፅ፣ ስህተት የሆነ ነገርን ማድረግ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አለማክበር ኃጢያት ነው። ኃጢያትን በትንሹ ከሰው ልጅ እይታ እንጀምር።

*ኃጢያት ምንድን ነው?*

*የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ አለማክበር ነው።*

ኃጢያትን የምንገነዘበው በአስተሳሰባችን መሰረት ነው:: ቢሆንም ግን፣ የሰው ልጅ የሚሰጣቸው ደረጃዎች እንደ ማህበራዊ መሰረቱ፣ የአእምሮ ሁኔታ፣ በተሰጡ ሁኔታዎችና አስተሳሰብ የተነሳ የተለያዩ ናቸው::

በዚህም የተነሳ ለኃጢያት የሚሰጠው ትርጉም ከሰው ሰው የተለያየ ነው:: አንደ አይነት ድርጊት እንደየሰዉ ለኃጢያት የሰጡት የደረጃ ሁኔታ ከኃጢያት ሊቆጠርም ላይቆጠርም ይችላል:: ለዚህም ነው እግዚአብሔር 613 አንቀጾችን ለኃጢያት መለኪያ ደረጆዎችን የሰጠን::

ከዚህ በታች ያለው ምስል የሰው ልጆችን ኃጢያት ያብራራል::




ከአስተሳሰባችንና ከማህበራዊ ሁኔታችን በመነሳት መቼም ቢሆን የኃጢያትን ደረጃዎች ልንሰጥ አንችልም::

በአስተሳሰባችን ኃጢያት የምንላቸው እግዚአብሔር ኃጢያት ብሎ ከዘረዘራቸው ጋር ላይሄዱ ይችላሉ:: ስለዚህም፣ አስተሳሰባችንን ማድመጥ የለብንም፣ ከዚህም ይልቅ እግዚአብሔር ባወጣቸው የኃጢያት መስፈርቶች መመርኮዝ አለብን::

ሁላችንም ስለኃጢያት የራሳችን የሆነ ግንዘቤ አለን:: ጥቂቶች የራሳቸው ጥፋት እንደሆነ አድርገው ሲወስዱት ሌሎቹ ደግሞ ከተዛባ ባህሪያቸው የመጣ አድርገው ይወስዱታል::

ለምሳሌ ኮርያ ውስጥ፣ ሰዎች የቤተሰቦቻቸውን መቃብር በሳር ይሸፍኑትና ሳሩን እስከ እለተ ሞታቸው ቀን ድረስ እንዲጠነቀቅላቸው ይዘውት ይዞራሉ:: በፓፑዋ፣ ኒው ጊኒ የገጠር ቦታዎች የሚኖሩ ጎሳዎች ደግሞ የሙት ቤተሰቦቻቸውን ክብር ለመግለፅ በሞቱ ቤተሰቦቻቸው አካል

ዙሪያ በመደነስ ይገልፁታል። (ካራካሱን ከመብላታቸው በፊት ስለማብሰላቸው እርግጠኛ አይደለሁም።) አካሉን በትል ከመበላት ለማዳን ፈልገው እንደሆነ አምናለሁ። ይህም የሰው ልጅ ስለ ኃጢያት ያለው አስተሳሰብ በጣም የተለያየ መሆኑን ይገልፃል።

በአንድ ማህበረሰብ እንደ ደግነት የሚቆጠር ተግባር በሌላ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ክፋት ሊቆጠር ይችላል። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢያት ማለት የእግዚአብሔርን ህግ አለማክበር መሆኑን ይነግረናል። *«የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጥሳችሁ፣ ጽዋን ማድጋንም እንደማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ። ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ። እንዲሁም አላቸው፦ ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል። »* (ማርቆስ 7፣8-9) የኛ አካላዊ ገፅታ በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዋጋ የለውም፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር በቀጥታ ወደ ውስጥ ልባችንን ማየት ይችላልና።

**የአንድ ሰው የግል መስፈርቶች በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያት ናቸው**

*በጣም አደገኛው*
*ኃጢያት ምንድን ነው?*

*የእግዚአብሔርን ቃል*
*አለማክበር ነው።*

በእግዚአብሔር ፊት እንደፍቃዱ አለመኖር ራሱ ኃጢያት ነው። በቃሉ አለማመንም እንደዚሁ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በመተው የራሳቸውን የባህል ትምህርቶች በመውሰድ እንደሚኖሩት ፈሪሳውያን መኖርም በራሱ ኃጢያት መሆኑን እግዚአብሔር ይናገራል። ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ወግ አጥባቂዎች እንደሆኑ ይቆጥራቸዋል።

«በየትኛው እግዚአብሔር ነው የምታምኑት? እኔን በትክክል ትቀበሉኛላችሁ እንዲሁም ታምኑኛላችሁ? በስሜ ትለፈልፋላችሁ፣ ሆኖም ግን በእውነት ታከብሩኛላችሁ?» ሰዎች ቃሉን በመተው ከላይ የሚታዩትን ይመስላሉ። በጣም ከፍተኛው ኃጢያት ቃሉን አለማክበር ነው። ይህን ታውቃላችሁን?

ከድክመቶቻችን የሚመነጩት ህገወጥ ድርጊቶች መውደቂያችን ናቸው:: ፍጹም ካለመሆናችን የምንፈጽማቸው ጥፋቶችና መጥፎ ድርጊቶች በመሰረታዊነት ኃጢያት አይደሉም፣ እነዚህ ስህተት ናቸው:: ምንም እንኳን ምንም አይነት ስህተት ባይኖርባቸውም የእርሱን ቃል የማያከብሩ ኃጢያተኞች ናቸው:: በእግዚያብሔር ፊት ታላቅ ኃጢያተኞች ናቸው:: ለዚህም ነው ኢየሱስ ፈሪሳውያንን ያስጠነቀቀው::

በመፅኃፍ ቅዱስ፣ ከፍጥረት እስከ ራዕይ ምን ማድረግ እንዳለብንና ምን ማድረግ እንደሌለብን የሚያስተምሩ ትዕዛዛት አሉ:: እነዚህም የእግዚአብሔር ቃላት፣ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ናቸው:: 100% ልናከብራቸው አንችል ይሆናል፣ ሆኖም ግን የእርሱ ትዕዛዛት መሆናቸውን ማስተወስ መቻል አለብን:: እርሱ ከመጀመሪያው ጀምሮ ስለሰጠን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ማክበር አለብን::

*«በመጀመሪያ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር::»* በመቀጠልም እንዲህ አለ:- *«ብርሃን ይሁን አለ፣ ብርሃንም ሆነ::»* ሁሉንም ነገር ፈጠረ:: በመጨረሻም ህግን አፀደቀ::

«ቃልም ስጋ ሆነ፣ ጸጋና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣» (ዮሐንስ 1:14) እንዴት? እግዚአብሔር ራሱን ለኛ አሳይቶአልን? ራሱን በትዕዛዛቱ አሳይቶአል:: ምክንያቱም እርሱ መንፈስና ቃል ነውና:: ስለዚህም፣ መጽሐፍ ቅዱስን ምን ብለን እንጥራው? የእግዚአብሔር ቃል ብለን እንጠራዋለን::

እንዲህም ተብሏል:- «የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ወደ ጎን በመተው፣ የሰው ልጅን ባህል ይዛችኋል:: በህጉ ውስጥ 613 አንቀፆች አሉ:: ይህን አድርጉ፣ ያን አታድርጉ፣ ቤተሰቦቻችሁን አክብሩ ወዘተ...:: በዘሌላውያን፣ ወንዶችና ሴቶች ምን ማድረግ እንዳለባቸው፣ ለማዳ እንስሳት ቦይ ውስጥ ቢወድቁ ምን ማድረግ እንዳለባቸው............. እነዚህን የመሳሰሉ 613 አንቀፆች በህጉ ውስጥ አሉ::

የሰው ልጆች ቃላትም ስላልሆኑ፣ በተደጋጋሚ ስለነሱ ማሰብ አለብን:: ሆኖም ሁሉንም ህግጋቱን ለመጠበቅ ባንችልም እንኳዋን ቢያንስ ቢያንስ ህጎቹን ማወቅና እግዚአብሔርን መታዘዝ መቻል አለብን::

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ትክክል ያልሆነ አንድ አንቀፅ እንኳን አለን? ፈሪሳውያን የእግዚአብሔርን ህግ በመተው የሰው ልጆችን ባህል ከህጎቹ አስበልጠዋቸዋል። የሽማግሌዎቻቸው ቃላት ከእግዚአብሔር ቃላት የበለጡ የከበዱ ሆነዋል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ የመሰከረውም ይህን ነበር፣ በጣም ያሳመመው ነገርም ሰዎች የእግዚአብሔርን ህግ መተዋቸው ነው።

እግዚአብሔር 613 አንቀፆችን የሰጠን እኛ ኃጢያቶቻችንን እንድናገናዝብና እርሱ እውነተኛና ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑን ለማሳየት ነው። ሁላችንም በሱ ፊት ኃጢያተኞች ስለሆንን፣ በእምነት መኖርና እግዚአብሔር እኛን ስለሚወደን በላከው በኢየሱስ ማመን አለብን።

የእርሱን ቃል ወደ ጎን የሚያደርጉና በእርሱም የማያምኑ ኃጢያተኞች ናቸው። የእርሱን ቃል ሊጠብቁ ያልቻሉትም ኃጢያተኞች ናቸው፣ ሆኖም ግን የእርሱን ቃላት ወደ ጎን ማድረግ ግን ከሁሉ የበለጠ ኃጢያት ነው። እንደዚህ አይነቱን ከባድ ኃጢያት የሚሰሩት መድረሻቸው ገሃነም ይሆናል። በእግዚአብሔር ፊት፣ በእርሱ ቃል አለማመን ከፍተኛው ኃጢያት ነው።

## እግዚአብሔር ለኛ ህግጋትን የሰጠበት ምክንያት




እግዚአብሔር ለኛ ህግጋትን የሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው? ኃጢያታችንን ተገንዝበን ወደ እርሱ እንድንመለስ ለማድረግ ነው። 613 የህግ አንቀፆችን የሰጠን ኃጢያቶቻችንን እንድናገናዝብና በኢየሱስ ክርስቶስም ምህረትን እንድናገኝ ነው። እግዚአብሔር ትዕዛዛትን ለኛ የሰጠበት ምክንያት ይህ ነው።

*ሮሜ 3:20 «ኃጢያት በህግ ይታወቃልና»* እንዲህ ይላል:: ስለሆነም፣ እግዚአብሔር ህግን የሰጠበት ምክንያት በህጉ እንድናድር ለማስገደድ እንዳልሆነ እናውቃለን::

እናስ፣ ከህግ የምናገኘው እውቀት ምንድን ነው? ይህም እኛ በእርሱ ፊት የኃጢያት መቃብርና በጣም ደካሞች ከመሆናችንም የተነሳ ህጉን ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ያለመቻላችንን ለማሳየት ነው:: ከ613ቱ የእርሱ ህጎች ምን እንገነዘባለን? ከዚህ የእኛን ድካምና በእርሱ ትዕዛዝ ለመኖር ያለመቻላችንን እንገነዘባለን:: እኛም የሰው ልጆች፣ የእግዚአብሔር ፍጡራን የሆንን ደካማ ፍጡራንና በእርሱ ፊትም የኃጢያት መቃብር መሆናችንን እንገነዘባለን:: በህጉ መሠረት ከሆነም የሁላችንም መጨረሻ የሚሆነው ገሃነም ነበር::

ኃጢያቶቻችንንና በህጉ መሠረት ለመኖር ያለመቻላችንን ከተገነዘብንስ፣ ምን እናደርጋለን? ሙሉ ሰዎች ለመሆን እንሞክራለን? አይደለም:: ኃጢያተኞች መሆናችንን መቀበልና በኢየሱስ ማመን፣ በእርሱ የውኃና የመንፈስ ድነት ምህረትን ማግኘትና ማመስገን አለብን::

እርሱ ህግጋትን የሰጠበት ምክንያት ኃጢያቶቻችንን እንድንቀበልና ለእነርሱም መክፈል የሚገባንን ፍርድ እንድናውቅ ነው:: ከዚያም፣ ከኢየሱስ ውጭ ከገሃነም የሚተረፍ አለመሆኑን እናውቃለን:: ኢየሱስ አዳኛችን መሆኑን ስናምን፣ ምህረት ይደረግልናል:: እርሱ ህግን የሰጠን ወደ አዳኙ ኢየሱስ እንዲመራን ነው::

እግዚአብሔር ህግን የፈጠረው፣ ምን ያህል ኃጢያተኞች እንደሆንን እንድናውቅና ከእንደነዚህ አይነት ኃጢያቶችም ነፍሳችንን እንድናድናት ነው:: ህግን ሰጥቶን በመቀጠልም የእርሱን አንድያ ልጅ ልኮ በጥምቀቱ ኃጢያታችንን ሁሉ እንዲቀበል አደረገ:: በእርሱ ማመንም ያድነናል::

እኛ በኢየሱስ ማመን ያለብንና የእግዚአብሔር ልጆች በመሆን ወደ እግዚአብሔር መንግስት መመለስ ያለብን ኃጢያተኞች ነን::

ሁሉም ነገር ከእርሱ የመጣ ስለሆነ፣ ነገሮችን መረዳት፣ ማሰብና መፍረድ ያለብን ከእርሱ ህግ አንፃር ነው::

ምህረቱንም ከቃሉ መረዳት አለብን፡፡ ይህ ትክክለኛ ውና እውነተኛው እምነት ነው፡፡

## በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ያለው ምንድን ነው?




እምነት መጀመር ያለበት በእግዚአብሔር ቃል ነው፣ እንዲሁም በቃሉ መሰረትም በእርሱ ማመን አለብን፡፡

ፈሪሳውያኑና ፀሃፍቱ የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በቆሻሻ እጃቸው ዳቦ ሲበሉ ሲያዩ፣ ከእግዚአብሔር ህግ አንፃር ቢመለከቱኣቸው ኑሮ ባልተጠየፏቸው ነበር፡፡ ቃሉ ወደ አፍ የገባ ነገር ሁሉ ሰውን ሳይጎዳ እሱንም ሆነ እሷን ምንም ሳያደርጋቸው በጨጓራ አልፎ ልብን ሳይነካ ከሰውነት እንደሚወጣ ይናገራል፡፡

በማርቆስ 7:20-23 እንደተፃፈውም፣ *«እርሱም አለ፣ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው፡፡ ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣው ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትእቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል፡፡»* ኢየሱስ ሰዎች ኃጢያተኛ ሆነው ስለተወለዱ ኃጢያተኞች መሆናቸውን ይነግረናል፡፡

ይህ ምን እንደሆነ ተረድታችሁታልን? ሁላችንም ስንወለድ ኃጢያት አለብን፣ ይህ የሆነበት ምክንያትም ሁላችንም የአዳም ዘሮች በመሆናችን ነው፡፡ ሆኖም ግን እውነታውን ለማየት ያልቻልነው በሁሉም ሙሉ ቃላቱ ስለማናምን ወይም ስለማንቀበል ነው፡፡ ከዚያስ፣ በሰው ልጅ ልብ ውስጥ ያለ ምንድን ነው?

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አንጽ ላይ:- «*ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣው ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ስድብ፣ ትእቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::* እነዚህ ኃጢያቶች በሙሉ ከሰው ውስጥ የሚወጡና ሰውንም የሚያረክሱ መሆናቸውን ያስረዳል::

በመዝሙረ ዳዊት ላይ እንደተጻፈውም:- *«የጣቶችህን ስራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፣ ጨረቃና ከዋክብትን አንተ የሰራኻቸውን፣ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጎበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?» (መዝሙር 8:3-4)*

እግዚአብሔር ራሱ የጎበኘን ለምንድን ነው? የጎበኘን ስለሚወደን፣ ስለፈጠረንና በኛ በኃጢያተኞቹ ስለተቀየመ ነው:: ኃጢያቶቻችንን ሁሉ ይቅር ብሎ የራሱ ሕዝቦች አድርጎናል:: *«አ ጌታ፣ የኛ ጌታ፣ ስምህ በመላ ምድርና ሰማይ ምን ያህል ድንቅ ነው!»* ብሎ ንጉስ ዳዊት በመዝሙሩ ላይ እግዚአብሔር ኃጥኣንን ለማዳን እንደሚመጣ ባወቀ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ዘምሯል::

በአዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ጳውሎስ ተመሳሳዩን መዝሙር ደግሞታል:: እኛ የእግዚአብሔር ፍጡራን የፈጣሪ ልጆች መሆናችን በጣም የሚደንቅ ነገር ነው:: ይህ ሊሆን የሚችለው በእርሱ ርህራሄ የተነሳ ነው:: ይህ የእግዚአብሔር ፍቅር ነው::

ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ህግ መሠረት እንኑር ማለት በራሱ እንደመፈታተን ሊሆን ነው:: ይህም በኛ ቸልተኝነት የሚመጣ አስቸጋሪ ትዕዛዝ ነው:: ህጉን በመጠበቅና ለራስ ብቻ እየጸለዩ ለብቻ መኖር፣ ፍቅሩን በመተው በራሱ አንድ ትክክል ያልሆነ ነገር ነው:: የእግዚአብሔር ፍላጎት፣ ራሳችንን እንደኃጢያተኞች ቆጥረን በህጉ መሰረት መኖርና በኢየሱስ ውኃና ደም ምህረትን እንደምናገኝ አምነን መኖር ይገባናል::

በማርቆስ ወንጌል 7:20-23 እንደተጻፈውም:- *«እርሱም አለ፣ ከሰው የሚወጣው ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣው ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትእቢት፣ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»*

ኢየሱስም ከሰው ልጆች የሚወጣ፣ ከውስጥ ያለ ኃጢያት እሱን/እሷን እንደሚረክስ ተናግሯል:: እግዚአብሔር የሰጠን ንጹህ ያልሆነ ምግብ እንኳን አያረክሰንም:: ፍጡራን በሙሉ ንጹህ ናቸው፣ ሆኖም ግን ከሰው ልጅ ውስጥ የሚወጣ፣ ይህም ኃጢያት ብቻ ነው ሊያረክሰን የሚችለው:: ሁላችንም ስንወለድ የአዳም ዘሮች ሆነን ነው:: ስለዚህም የምንወለደው ከምን ጋር ነው? የምንወለደው ከ12 አይነት ኃጢያቶች ጋር ነው:: ይህ ትክክል አይደለምን?

እናስ ኃጢያት ሳንሰራ መኖር እንችላለን? ከኃጢያት ጋር ስለተወለድን ኃጢያት መስራታችንን እንቀጥላለን:: ህጉን ብቻ ስለምናውቅ ኃጢያት መሥራት እናቆማለን? በትዕዛዛቱ መሰረትስ ልንኖር እንችላለን? በፍፁም::

የበለጠ በህጉ መሠረት ለመኖር በፈለግን ቁጥር የበለጠ አስቸጋሪ እየሆነብን ይመጣል:: ገደባችንን ማወቅና ያለፉ ነገሮቻችንን መተው መቻል አለብን:: ከዚያም በንጹህ አእምሮአችን የኢየሱስን ጥምቀትና ደም እንቀበላለን፣ ይህም ያድነናል::

የህጉ 613 አንቀጾች በሙሉ ጥሩና ትክክል የሆኑ ናቸው:: ሆኖም ግን ሰዎች ገና በእናታቸው ማህጸን ሳሉ ጀምሮ ኃጢያተኞች ናቸው:: የእግዚአብሔር ህግ ትክክል መሆኑን ካወቅንና፣ ሆኖም ግን ኃጢያተኞች ሆነን ስለተፈጠርን መቼም ቢሆን በራሳችን ፍጹም መሆን እንደማንችል ካመንን፣ በኢየሱስ ጥምቀት፣ ደምና መንፈስ ወንጌል በማመን የእግዚአብሔርን ምህረት ማግኘት እንዳለብን ወደመገንዘብ እንመጣለን:: ገደቦቻችንን ስናውቅ-- ፍጹም አለመሆናችንን እና ለዚህም ወደ ገሃነም እንደምንገባ እንረዳለን-- ሆኖም ግን በኢየሱስ ምህረት አናምንም::

ልንድን እንችላለን:: እኛ በራሳችን በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ወይም ትክክል ልንሆን እንደማንችል መገንዘብ መቻል አለብን:: ስለሆነም፣ በእግዚአብሔር ፊት ሁላችንም ኃጢያተኞች በመሆናችንና ወደገሃነም እንዳንገባ «እግዚአብሔር፣ እባክህን ከኃጢያቴ አድነኝ፣ ምህረትንም አድርግልኝ» ብለን መጸለይ ይኖርብናል:: በመቀጠልም እግዚአብሔር በቃሉ መሰረት ይገናኘናል:: በዚህ መሰረትም ልንድን እንችላለን::

*የዳዊትን ጸሎት እንመልከት:- «የሚያጠፋ ቃልን ሁሉ፣ የሽምገላ ቃልን ወደድህ::» (መዝሙር 51:4)*

ዳዊት የሰራው ክፋት በሙሉ ብዙ ኃጢያት ስለነበር ወደ ገሃነም እንደሚከተው ያውቃል፣ በእግዚአብሔር ፊትም እንዲህ ብሏል፡- «ጌታ ሆይ፣ ኃጢያተኛ ብለህ ብትጠራኝ፣ ኃጢያተኛ ነኝ:: ፍጹምም ብትለኝ፣ ፍጹም ነኝ:: ብታድንኝ እድናለሁ፣ ወደ ገሃነም ብትልከኝም፣ መጨረሻዬ ገሃነም ይሆናል::»

ይህ ትክክለኛው እምነትና የመዳኛ መንገድ ነው:: በኢየሱስ ምህረት የምናምን ከሆነ መሆን የሚገባን እንዲህ ነው::

## ኃጢያቶቻችን ምን እንደሆኑ በትክክል ማወቅ አለብን

ሁላችንም የአዳም ዘሮች ስለሆንን፣ በልባችን ኃጢያቶች አሉብን:: ሆኖም ግን፣ እግዚአብሔር ምን ይነግረናል? ምንም እንኳን በልባችን ውስጥ አመንዝራነት ቢኖርም አመንዝራዎች መሆን የለብንም:: በልባችን ውስጥ ጭካኔ አለ፣ እግዚአብሔር ግን ምን ይለናል? እግዚአብሔር መግደል እንደሌለብን ይነግረናል:: ሁላችንም በልባችን ለቤተሰቦቻችን ክብር እንደሌለን እናውቃለን፣ እግዚአብሔር ግን ቤተሰቦቻችንን ማክበር እንዳለብን ይነግረናል:: የእግዚአብሔር ቃል ትክክልና ጥሩ እንደሆነ፣ እንዲም እኛም ሁላችንም ኃጢያት በልባችን እንዳለብን ማወቅ አለብን::

ይህ ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ይህ ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው:: ስለዚህስ፣ በእግዚአብሔር ፊት ምን ማድረግ አለብን? ሁላችንም የኃጢያት ክምችቶችና ተስፋ የሌለን ኃጢያተኞች መሆናችንን ማመን አለብን:: ትላንትና ምንም ኃጢያት ስላልሰራን ትላንት ፍጹም እንደነበርንና ዛሬ ደግሞ ኃጢያት ስለሰራን ዛሬ ኃጢያተኞች እንደሆንን አድርጎ ማሰብም ትክክል አይደለም:: ስንወለድም ጀመሮ ኃጢያተኞች ነበርን:: ምንም ነገር ብንሰራም፣ አሁንም ድረስ ኃጢያተኞች ነን:: በኢየሱስ ጥምቀት በማመን ምህረትንም የምንሻው ለዚህ ነው::

ኃጢያተኞች የሆንነው በምንሰራው ስራ አይደለም፣ ማለትም ማመንዘር፣ መግደል፣ መስረቅ፣...... ወዘተ.. ሆኖም ግን ኃጢየተኞች የሆንነው ኃጢያተኞች ሆነን ስለተወለድን ነው:: የተወለድነው ከ12 አይነት ኃጢያቶች ጋር ነው፣ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት ከተወለድን ጀምሮ

ኃጢያተኞች ነን፣ በራሳችን ጥረት ጥሩዎች መሆን አንችልም:: መሆን የምንችለው ጥሩ እንደሆንን መምሰል ብቻ ነው::

ከኃጢያተኛ አእምሮ ጋር ተወልደን፣ በእርግጥም ኃጢያት የማንሰራ ስለሆነ ብቻ እንዴት ፍጹም ልንሆን እንችላለን? በራሳችን በእግዚአብሔር ፊት መቼም ፍጹም ልንሆን አንችልም:: ፍጹም እንደሆንን የምናስብ ከሆነም፣ ተመጻዳቂዎች ነን ማለት ነው:: ኢየሱስ ፈሪሳውያንንና ፀኃፍትን «ተመጻዳቂዎቹ ፈሪሳውያንን ፀኃፍት» ብሎ ይጠራቸዋል:: የሰው ልጆች ኃጢያተኞች ሆነው ስለተወለዱም ለዘላለምም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያትን እየሰሩ ይኖራሉ::

ማንም ሰው እሱ/እሷ ያልተጣሉ፣ ማንንም ያልደበደቡ፣ ያልሰረቁ ወይም አንዲት መርፌ እንኳን የሰውን በህይወት ዘመናቸው ያልወሰዱ መሆናቸውን ቢናገሩም እየዋሹ ነው፣ ምክንያቱም የሰው ልጆች ከተወለዱ ጀምሮ ኃጢያተኞች ናቸውና:: ይህ ሰውም ውሸታም፣ ኃጢያተኛ ና ተመጻዳቂ ነው:: እግዚአብሔር እሱን/እሷን የሚመለከተው እንደዚህ ነው::

ማንም ሰው ከተወለደበት/ችበት ቀን ጀምሮ ኃጢያተኛ ነው:: ምንም እንኳ አንዲት ቅንጣት ኃጢያት ባትሰሩም፣ የምትሄዱት ወደ ገሃነም ነው:: ምንም እንኳን ትዕዛዛቱን ብትጠብቁም፣ አሁንም ድረስ ወደ ገሃነም የምትሄዱ ኃጢያተኞች ናችሁ::

ከዚያስ፣ ከነዚህ ነገሮች ለመዳን ምን ማድረግ አለብን? ከኃጢያታችን ለመዳን በእርሱ ላይ ተመክተን ይቅርታን መለመን አለብን:: እርሱ ካላዳነን የምንሄደው ወደ ገሃነም ነው:: ይህም የኛ ድርሻ ነው::

ኃጢያተኞች መሆናቸውን የተቀበሉ ብቻ ናቸው የእግዚአብሔር ቃልን የሚቀበሉት:: እነርሱም ፍጹም የሚሆኑት በእምነት ብቻ መሆኑን ያውቃሉ:: ስለዚህም ቃሉን ባለማክበርና ወደጎን በማድረግ መኖርም ከፍተኛው ኃጢያት መሆኑን ያውቃሉ:: ቃሉን የሚቀበሉ፣ ምንም እንኳን በፊት ኃጢያተኞች ቢሆኑም ፍጹም ናቸው:: እነርሱ በቃሉ መሠረት እንደገና የተወለዱና በምህረቱም የተባረኩ ናቸው::

## በስራቸው ምህረትን ለማግኘት የሚሹ ሁሉ ኃጥኣን ናቸው




ገላትያ 3፡10 እና 11 ን እናንብ፡- *«ከሕግ ስራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፣ በሕግ መጽሐፍት በተፃፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም፣ ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎኣልና። ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ ግልፅ ነው።»*

እንደተባለውም...... *«በሕግ መጽሐፍት በተፃፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም፣ ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎኣልና።»* በኢየሱስ የሚያምኑ የሚመስላቸውና፣ በስራቸውም እንዲፈረድላቸው የሚፈለጉ ሰዎች የተረገሙ ናቸው። በስራቸው እንዲፈረድላቸው የሚፈልጉት ያሉት የት ነው? በእግዚአብሔር መርገምት ስር ናቸው።

እግዚአብሔር ሕግን የሰጠን ለምንድን ነው? እርሱ ሕግን የሰጠን ኃጢያቶቻችንን እንድናገናዝብ ነው። (ሮሜ 3፡20) እርሱም እኛ በኃጢያት የተሞላንና የሚገባንም ገሃነም መሆኑን እንድናውቅ ይፈልጋል።

በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ እመኑ፣ ከውኃና ከመንፈስም እንደገና ተወለዱ። ከዚያም፣ ከኃጢያታችሁ ሁሉ ትነፃላችሁ፣ ፍጹምም ትሆናላችሁ፣ ወደ ገነት በመግባትም ዘላለማዊ ህይወትን ትጎናጸፋላችሁ። ከልባችሁ እምነት ይኑራችሁ።

## በአለም ላይ በጣም መጥፎው ኃጢያት

*በአለም ላይ ከባዱ*
*ኃጢያት ምንድን ነው?*

*በሕጉ መሰረት ለመኖር*
*መሞከር።*

በእርሱ በረከት እምነት ስላለን እኛም የተባረክን ነን። እግዚአብሔር በእርሱ ቃል እምነት ያላቸውን ያድናል።

ሆኖም ግን ዛሬ፣ ከአማኞች መካከል፣ በሕጉ መሠረት ለመኖር የሚፈልጉ ብዙ ክርስትያኖች አሉ። በሕጉ መሠረት ለመኖር መፈለጋቸው በጣም ጥሩ ቢሆንም፣ እንዴት ሊኖሩ ይችላሉ?

በቃሉ መሠረት ለመኖር መፈለግ ማለት ምን ያህል የሞኝነት ተግባር እንደሆነ መገንዘብ አለብን። የበለጠ በሞከርን ቁጥር፣ የበለጠ አስቸጋሪ እየሆነ ይመጣል። *«እምነት ከማድመጥ ይመጣል፣ ማድመጥም በእግዚአብሔር ቃል ነው»* ይላል። ለመዳን ያለንን ክፋት ማስወገድ አለብን።

## ለመዳን የራሳችንን መስፈርቶች መተው አለብን

*ለመዳን ምን*
*ማድረግ አለብን?*

*የራሳችንን መስፈርቶች*
*መተው መቻል አለብን።*

ሰው እንዴት ሊድን ይችላል? ይህ ሊሆን የሚችለው እሱ/እሷ ራሱን/ራሷን ኃጢያተኛ እንደሆኑ አድርገው ማሰብ ከቻሉ ብቻ ነው። እስካሁንም ድረስ ለተሳሳተ እምነትና ለራሳቸው ጥረት ባላቸው ፍላጎት የተነሳ ምህረትን ያላገኙ አሉ።

እግዚአብሔር ወደ ሕጉ ጣታቸውን የሚጠቁሙ ሁሉ የተረገሙ ናቸው ይላል። እነዚያ በኢየሱስ ካመኑ በኋላ ቀስ

በቀስ በሕጉ መሰረት በመኖር ፍጹም እንደሚሆኑ የሚያምኑት የተረገሙ ናቸው:: በእግዚአብሔር ያምናሉ፣ ሆኖም ግን ለመዳን በሕጉ መሠረት መኖር እንዳለባቸው ያስባሉ::

ውድ ጓደኞቼ በስራችን ፍጹም ልንሆን እንችላለን? ፍጹም ልንሆን የምንችለውና ለኃጢያታችንም ምህረትን ለማግኘት የምንችለው በኢየሱስ ስናምን ብቻ ነው:: በኢየሱስ ጥምቀት በደሙና በእግዚአብሔርነቱ በማመን ብቻ ነው ምህረትን ልናገኝ የምንችለው::

እግዚአብሔርም የህግን እምነት ለኛ ያዘጋጀበት ምክንያቱ ፍጹም እንድንሆን ነው:: በውኃና በመንፈስ የሚገኝ ምህረት የሚመረኮዘው በሰዎች ስራ ላይ ሳይሆን ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል ባላቸው እምነት ላይ ነው:: እግዚአብሔር የላከን በእምነት ነው፣ እግዚአብሔር ድነታችን እንዲሟላም የሚፈልገው በዚሁ ነው::

በኢየሱስ የሚያምኑትስ ምህረትን የማያገኙት ለምንድን ነው? ምክንያቱም የውኃና የመንፈስን ምህረት ቃል ስለማይቀበሉት ነው:: እኛ ግን፣ እነሱ እንደነበሩት ፍጹም ያልነበርነው፣ በእግዚአብሔር ቃል ባለን እምነት መሰረት ምህረትን አግኝተናል::

ሁለት በድንጋይ መፍጫ ላይ የሚሰሩ ሰዎች፣ ወደ ኋላ የቀረው ሰው መስራት አለበት ምንም እንኳን አንደኛ ው ቢጨርስም:: ወደ ኋላ የቀረው ሰው ገና ምህረት ያላገኙትን ሰዎች ያመለክታል:: አንደኛው ተወስዶ ሌላኘው ወደ ኋላ የቀረው ለምንድን ነው?

ምክንያቱ አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል ያደመጠና ያመነ ሲሆን፣ ሌላኛው ግን የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጠበቅ ጠንክሮ የሰራ ቢሆንም ቀስ በቀስ ወደ ገሃነም የወረደ ስለሆነ ነው:: ይኸኛው ሰው በመንጠላጠል ወደ እግዚአብሔር ለመውጣት የፈለገ ሲሆን፣ ልክ በእግር ላይ እንደተንጠለጠለ፣ እግዚአብሔር ወደ ታች ለቀቀው:: አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ህግ በመጠበቅ ወደ ላይ ለመንጠልጠል ቢፈልጉ፣ በእርግጠኝነት እሱ/እሷ ወደ ገሃነም ይወረወራሉ::

በውኃና በመንፈስ እምነት ኖሮን ምህረት እንዲደረግልን የተፈለገው ለዚህ ነው::

*«ከሕግ ስራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች ናቸውና፣ በሕግ መጽሐፍት በተፃፉት ሁሉ ጸንቶ የማይኖር የማያደርግም፣ ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና:: ጻድቅ*

*በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንደማይጸድቅ ግልፅ ነው።»«ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደተጻፈ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጻልና።» (ገላትያ 3:10-11፣ ሮሜ 1:17)*

በእግዚአብሔር ቃል አለማመን በእርሱ ፊት ኃጢያት ነው። በተጨማሪም፣ በራሳችን መስፈርት መሰረት የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ጎን ማድረግም ኃጢያት ነው። እኛ የሰው ልጆች ከተወለድን ጀምሮ ኃጢያተኞች ስለሆንና በህይወታችንም ሙሉ ኃጢያትን መስራት ስለማናቆም፣ በሕጉ መሰረት ልንኖር አንችልም። እኛ በሄድንበት ቦታ ሁሉ፣ አንዱ ጋ ትንሽ፣ አሁንም ትንሽ እያልን ብዙ ኃጢያት እንሰራለን። ስጋ መሆናችንንና ከኃጢያት ውጭ ምንም ማድረግ የማንችል መሆናችንን መገንዘብ ያስፈልገናል።

እኛ የሰው ልጆች ልክ በእዳሪ የተሞላ ቅርጫት አይነት ነን። ልንሸከመው ብንፈልግ በመንገዱ ሁሉ ይንጠባጠባል። ልክ እንደዚህ ነን። በየሄድንበት ቦታ ሁሉ ኃጢያትን እናደርጋለን። ይህን በሃሳባችሁ ልትስሉት ትችላላችሁን?

አሁንም ድረስ ቅዱስ የሆናችሁ ይመስላችኋልን? ስለራሳችሁ በትክክል ተረድታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ ቅዱስ ለመሆን የምታደርጉትን ጥረት ትታችሁ በኢየሱስ ውኃና ደም ታምኑ ነበር።

አሁንም ድረስ እንደገና ያልተወለዱት በእግዚአብሔር ፊት የኃጢያት መከማቻዎች መሆናቸውን ማመንና ያለባቸውን ኩራት መጣል አለባቸው። ከዚያም፣ ወደ ቃሉ ተመልሰው በውኃና በመንፈስ እንዴት እንዳዳናቸው ከቃሉ መረዳት አለባቸው።✉

## የሰው ልጆች የተፈጠሩት ኃጥኣን ሆነው ነው

**«ማርቆስ 7፡20-23»**

**«እርሱም አለ፡- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»**

## ሰዎች ተወናብደው በራሳቸው ድንበሩ ውስጥም ይኖራሉ




በመጀመሪያ ጥያቄ ልጠይቃችሁ እወዳለሁ:: ራሳችሁን የምታዩት እንዴት ነው? ጥሩዎች ወይስ መጥፎዎች እንደሆናችሁ ነው የምታስቡት? ምን ታስባላችሁ?

ብዙ ሰዎች በራሳቸው መደናበር ውስጥ ይኖራሉ:: የምታስቡትን ያህል መጥፎዎች ላትሆኑ ትችላላችሁ፣ የምታስቡትንም ያህል ጥሩዎች ላትሆኑ ትችላለችሁ::

በህይወት የበለጠ በጥሩ እምነት የሚኖረው የትኛው ይመስላችኋል? ራሱን/ራሷን ጥሩ እንደሆኑ አድርገው የሚስቡት ናቸውን? ወይስ ራሳቸውን መጥፎ እንደሆኑ አድርገው የሚያስቡት?

ሁለተኞቹ ናቸው:: ሌላም ጥያቄ ልጠይቃችሁ:: ከሁለቱ የበለጠ ምህረትን ሊያገኝ የሚችለው የትኛው ነው-- ብዙ ኃጢያቶችን የሰራው ነው ወይስ ጥቂት ኃጢያቶችን የሰራው ነው? ብዙ ኃጢያቶችን የሰራውና እሱ/እሷ የኃጢያት ጎተራ መሆናቸውን የሚያምኑት የበለጠ ምህረት የማግኘት እድል አላቸው፣ ምክንያቱም እነርሱ ብዙ ኃጥያቶችን መስራታቸውንና ኃጢያቶች መሆናቸውንም ስለሚያወቁ ነው::

እንደዚህ አይነቱ ሰው በኢየሱስ ለሱ/ለሷ የተዘጋጀላቸውን የምህረት ቃል በበለጠ ሁኔታ ይቀበላሉ።

ራሳችንን በትክክል ስንመለከት፣ ግዙፍ የኃጢያት ክምር መሆናችን ግልጽ ነው። የሰው ልጆች ምንድን ናቸው? ሰዎች «የክፋት ዘሮች» ናቸው። በኢሳያስ 59 ላይ፡- በሰዎች ልብ ውስጥ ሁሉም አይነት ክፋቶች መኖራቸውን ይናገራል። ስለዚህም፣ ሰዎች የኃጢያት ክምር መሆናቸው ግልፅ ነው። ሆኖም ግን፣ የሰው ልጆችን የኃጢያት ክምር ብለን ከገለፅናቸው፣ ብዙዎች አይስማሙም። ሆኖም ግን «የክፋት ዘሮች» ብለን ብንገልጻቸው ትክክለኛው ገለፃ ነው። በታማኝነት ወደ ራሳችን ብንመለከት፣ ክፉ ሰዎች መሆናችን ግልፅ ሆኖ ይታየናል። ለራሳቸው ታማኝ የሆኑ ሰዎች ለዚህ ተመሳሳይ የሆነ ማጠቃለያ ላይ ይደርሳሉ።

ነገር ግን፣ ብዙ ሰዎች የኃጢያት ክምር መሆናቸውን ሲቀበሉ አይታዩም። ብዙዎችም ራሳቸውን እንደ ኃጢያተኞች ስለማይቆጥሩ በምቾት ሲኖሩ ይታያሉ። እኛም ክፉዎች ስለሆንን፣ በኃጢያት የተሞላ ስልጣኔን ፈጥረናል። ይህ እውነት ባይሆን ኖሮ ኃጢያት መስራት ያሳፍር ነበር። ሆኖም ግን ብዙዎቻችን ኃጢያት ብንሰራም አናፍርም።

የማናችንም ቢሆን ሰብዕናችን ያውቃል። «የሚያሳፍር ነው» የሚላቸው ሰብዕና አላቸው። አዳምና ሔዋን ኃጥያትን ከሰሩ በኋላ ራሳቸውን ከዛፍ ስር ሸሸጉ። ዛሬም፣ ብዙ ኃጥኣን ራሳቸውን ከዚህ ጥፉ ባህል-- የኃጢያት ባህል ውስጥ ይሸሽጉታል። ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥም ራሳቸውን ከመሰሎቻቸው ኃጥኣን ጀርባ ይደብቃሉ።

ሰዎች በራሳቸው መደናበር የተነሳም ይሸወዳሉ። ራሳቸውን ከሌሎች የበለጡ ደጋጎች እንደሆኑ ያስባሉ። ስለዚህም፣ መጥፎ ዜና ሲሰሙ፣ በመጮህ «ሰው እንዴት እንደዚህ ያደርጋል? አንድ ሰው ይህን እንዴት ሊያደርግ ይችላል? እንዴት አንድ ልጅ በገዛ ቤተሰቦቹ ላይ እንደዚህ አይነት ስራ ይሰራል?» ሲሉ ይደመጣሉ። ራሳቸው ቢሆኑ ግን ያንን ነገር እንደማያደርጉት ያምናሉ።

ውድ ጓደኞቼ፣ ራሳችሁን ማወቅ ለናንተ በጣም ከባድ ነው። በትክክል ራሳችንን ለማወቅ፣ በመጀመሪያ ስለ ኃጢያት ምንነት ማወቅ ያስፈልገናል። በሰው ልጅ ተፈጥሮኣችን፣ ትክክለኛውን እውቀት ለማግኘት ረጅም

ጊዜ ይወስድብናል፣ ብዙዎችም እንዲሁ እስከሚሞቱበት ጊዜ ድረስ እንኳን ይህንን አያውቁትም::

## ራሳችሁን እወቁ

*ራሳቸውን የማያውቁ*
*የሚኖሩት እንዴት ነው?*

*ኃጢያተኛ ማንነታቸውን በመደበቅ*
*የተመጻደቀ ኑሮ ይኖራሉ::*

አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን በትክክል የማያውቁ ሰዎች ያጋጥሙናል:: ሶቅራጠስ እንዳለውም:- «ራሳችሁን እወቁ»:: ሆኖም ግን፣ ብዙዎቻችን በልባችን ውስጥ ምን እንዳለ አናውቅም፣ መግደል፣ ስርቆት፣ አለመታመን፣ ድክመት፣ መወሻሸት፣ መደባበቅ፣ መመቅኘት ወዘተ........

ራሱን የማያውቅ ሰው በውሸት ማር በተቀባ ከናፍሮቹ ስለ ጥሩነት ሲያወራ ይሰማል:: ለዚህ ምክንያቱ ይህ ሰው ሲወለድ ምን ያህል ኃጢያተኛ ሆኖ እንደተወለደ ስለማያውቅ ነው::

በዚህ አለም ላይ እውነተኛ ተፈጥሮአቸውን የማያውቁ ብዙ ሰዎች አሉ:: ራሳቸውንም ሸውደዋል፣ በራሳቸው ሸወዳ ውስጥም ሙሉ በሙሉ ተውጠው መኖር ይፈልጋሉ:: ራሳቸውን በመሸወዳቸው ራሳቸውን ወደ ገሃነም እየወረወሩት መሆናቸውን አያውቁትም::

## ሰዎች ኃጢያትን በህይወታቸው ሙሉ ይፈጽማሉ

*ወደ ገሃነም የሚገቡት*
*ለምንድን ነው?*

*ራሳቸውን ስለማያውቁ ነው::*

ማርቆስ 7:21-23ን እንመልከት:- *«እርሱም አለ:- ከሰው የሚወጣው፣ ሰውን የሚያረክስ ያ ነው:: ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ መጎምጀት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ መዳራት፣ ምቀኝነት፣ ስድብ፣ ትዕቢት ስንፍና ናቸውና፣ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፣ ሰውንም ያረክሰዋል::»* የሰው ልጆች ልብ ከተጸነሱበት ዕለት አንስቶ በኃጢያት የተሞላ ነው::

የሰው ልጅ ልብን እስከ አፉ ድረስ በቆሻሻ ውሃ ይህም በኃጢያት እንደተሞላ ብርጭቆ አድርገነው እንውሰድ:: ይህ ሰው ወደፊትና ወደ ኋላ ቢወዛወዝ የሚከሰተው ምንድን ነው? ቆሻሻው ውሃ (ኃጢያት) በየቦታው ይረጫል:: ሰውየው የበለጠ በተንቀሳቀሰ ቁጥር፣ ኃጢያት ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ በየቦታው ይረጫል::

እኛም፣ የኃጢያት ክምር የሆንነው፣ ህይወታችንን የምንኖረው ልክ እንደዚህ ነው:: በየሄድንበት ሁሉ ኃጢያትን እያሰራጨን እንሄዳለን:: የኃጢያት ክምሮችም ስለሆንን በህይወታችን ሁሉ ኃጢያትን እንሰራለን::

ችግሩ ግን እኛ የኃጢያት ክምር መሆናችንን አለማወቃችን ነው፣ ወይም በሌላ ቃላት የኃጢያት ዘሮች መሆናችንን አለማወቃችን ነው:: ከተወለድንበት እለት ጀምሮ የኃጢያት ክምርና በልባችንም ኃጢያት ያለብን ነን::

ይህ የኃጢያት ክምርም ለመፍሰስ የተዘጋጀ ነው:: ሆኖም ግን፣ ሰዎች በዘር ኃጢያተኞች መሆናቸውን አያምኑም:: የሚያስቡትም ሌሎች ወደ ኃጢያት እንደመሯቸው ነው፣ በዚህም የተነሳ እነሱ ሳይሆኑ ሌሎቹ መጥፎዎች እንደሆኑ ያስባሉ::

ኃጢያትን እየሰሩም እንኳን፣ አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ኃጢያት ነጻ ለመሆን የሚጠበቅባቸው ንስሐ መግባት ብቻ እንደሆነ ያስባሉ:: በሚሰሩት ኃጢያ ሁሉም ይህ የነሱ ስህተት እንዳልሆነ በማሰብ ራሳቸውን ያታልላሉ:: ራሳችንን ማንጻት ስለምንችል ብቻ እየቆሸሽን መኖር አለብን? በተደጋጋሚ መጥረግ ሊኖርብን ነው ማለት ነው::

ብርጭቆው በኃጢያት የተሞላ ጊዜ፣ መፍሰሱን ይቀጥላል:: ውጭውን መጥረጉ ምንም ጥቅም የለውም::

ምንም ያህል ጊዜ ውጭውን በጥሩ ነገር ብናፀዳውም፣ ውስጡ በኃጢያት የተሞላ ስለሆነ ምንም ጥቅም የለውም።

ከብዙ ኃጢያት ጋር ስለተፈጠርንም፣ ምንም ያህል ኃጢያት በየመንገዱ ብንጥልም ልባችን መቼም ንፁህ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም፣ በህይወት ዘመናችን ሁሉ ኃጢያትን እንፈፅማለን።

አንድ ሰው የኃጢያት ክምር መሆኑን እስካልተገነዘበ ድረስ፣ እሱ/እሷ የኃጢያተኛ ፍጥረታቸውን ለመደበቅ ይሞክራሉ። ኃጢያት በሁሉም ሰው ልብ ውስጥ ያለና ላዩን ብቻ በመጥረግ ሊጠፋ የሚችል ነገር አይደለም። ትንሽ ኃጢያት በጣልን ቁጥር፣ አንዴ በፎጣ፣ አንዴ ደግሞ በጨርቅ፣ እንዲሁም በመሳሰሉት ነገሮች እንጠርገዋለን። ይህን የምናደርገውም ደጋግመን በጠረግነው ቁጥር የበለጠ ንጹህ የሚሆን እየመሰለን ነው። እውነታው ግን፣ በተደጋጋሚ የሚፈስ ነገር ስለሆነ ሊጠራ የማይችል መሆኑ ነው።

ይህ ነገር እስከ መቼ ድረስ የሚቀጥል ይመስላችኋል? ያ ሰው እስኪሞት ድረስ እንዲሁ እያለ ይቀጥላል። ሰዎች እስከመሞቻ ቀናቸው ድረስ ኃጥያት መስራታቸውን ይቀጥላሉ። ለዚህም ነው ምህረት ለማግኘት በኢየሱስ ማመን ያለብን። ምህረት እንድናገኝ፣ በመጀመሪያ ራሳችንን ማወቅ አለብን።

*የኢየሱስን ፍቅር በበለጠ የሚያገኘው ማነው?*

*ብዙ ስህተቶችን መስራታቸውን የሚያውቁ ኃጢያተኞች ናቸው።*

ሁለት በሁለቱ በቆሻሻ ፈሳሽ በተሞሉ ብርጭቆዎች የሚመሰሉ ሁለት ሰዎች አሉ እንበል። ሁለቱም ብርጭቆዎች በኃጢያት የተሞሉ ናቸው። አንደኛው ወደ ራሱ ተመልክቶ «አ! እኔ በጣም ኃጢያተኛ ሰው ነኝ» ይላል። በመቀጠልም ይህን በመተው ከዚህ ለመውጣት የሚረዳውን ፍለጋ ይወጣል።

ሌላኛው ግን እርሱ በትክክል ክፉ መሆኑን አያምንም:: በውስጡ ያለውን የኃጢያት ክምርም ለማየት ስለማይችል፣ ራሱን ኃጢያተኛ እንዳልሆነ አድርጎ ያስባል:: በህይወቱ ሙሉም ያፈሰሰውን ሲጠርግ ይኖራል:: አንደኛውን ጎን ሲጠርግ ሌላው ይቆሽሻል፣ ሌላኛውን ጎን ሲያጠዳም ይህኛው ይቆሽሻል....... በዚህ ሁኔታም ይቀጥላል::

ሌሎች ደግሞ ሞልቶ እንዳይፈስ፣ በቻሉት መጠን የሚሰሩትን ኃጢያት ለመቀነስ በጥንቃቄ ለመኖር ይሞክራሉ:: ሆኖም ግን በልባቸው አሁንም ድረስ ኃጢያት ስላለባቸው፣ ይህ ምን ያህል ጥሩ ሊሆንላቸው ይችላል? ጥንቁቅ መሆን ወደ ገነት ምንም ያህል አያቀርባቸውም:: በተቃራኒው «መጠንቀቃቸው» ወደ ገሃነም ሊመራቸው ይችላል::

ውድ ጓደኞች፣ ጥንቁቅ መሆን የሚመራው ወደ ገሃነም እሳት ነው:: ይህን ትምህርት ወደ ልባችን ማስገባት አለብን:: ሰዎች ጥንቁቅ በሆኑ ቁጥር፣ ኃጢያታቸው ብዙም ሊፈስ የማይችል ሊሆን ይችላል፣ ሆኖም ግን አሁንም ድረስ ኃጥኣን ናቸው::

በሰው ልጆች ልብ ውስጥ ያለው ምንድን ነው? ኃጢያት? ተንኮል? አዎን! ክፉ ሃሳብ? አዎን! ሌብነትስ አለ? አዎን! ገፊኝነት? አዎን!

የኃጥያት ክምር የመሆናችን እውነታ በተለይም ማንም ሳያስተምረን ክፋትንና ምቀኝነትን ስንተገብር እውነታውን ከመቀበል ውጭ ምንም ልናደርግ አንችልም::

በወጣትነታችንን ያንን ያህል ጎልቶ አይወጣ ይሆናል:: ሆኖም ግን እያረጀን ስንሄድስ? ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤት፣ ወደ ኮሌጆችና ወደ መሳሰሉት ስንሄድስ፣ በውስጣችን ያለው ኃጥያት ብቻ መሆኑን እየተገነዘብን እንመጣለን:: ይህ እውነት አይደለምን? እውነቱን ለመናገር፣ ኃጢያተኛ ማንነታችንን ለመደበቅ አንችልም:: አይደል? ኃጥያትን ከማፍሰስ ውጭ ምንም ማድረግ አንችልም:: ከዚያም «ይህን ማድረግ አልነበረብኝም» እያልን እናማርራለን:: ሆኖም ግን፣ በእውነት ይህን ለመቀየር በጣም አስቸጋሪ ሆኖ እናገኘዋለን:: ይህ ለምን ሆነ? ምክንያቱ እያንዳንዳችን የተወለድነው የኃጢያት ክምር ሆነን ነው::

ጠንቃቆች በመሆን ብቻ ንጹህ ልንሆን አንችልም:: ሙሉ በሙሉ ምህረት እንድናገኝ የተወለድነው የኃጢያት ክምር ሆነን መሆኑን ማወቅ አለብን:: በኢየሱስ የተዘጋጀውን

ምህረት በታላቅ ሁኔታ ለመቀበል የተዘጋጁ ኃጥኣን ብቻ ናቸው ሊድኑ የሚችሉት።

«ብዙም ኃጢያት አልሰራሁም፣ ወይም ብዙም ስህተት አልሰራሁም» ብለው የሚያስቡት ግን ኢየሱስ ኃጢያታቸውን ሁሉ እንደሚያነጻላቸው ስለማያምኑ መጨረሻቸው የሚሆነው ገሃነም ነው። ሁላችንም የተወለድነው ከኃጢያት ጋር ስለሆነ የኃጢያት ክምር መሆናችንን ማመን አለብን።

አንድ ሰው «ብዙም ኃጢያት አልሰራሁም፣ ለዚህች ብቻ ምህረት የሚደረግልኝ ከሆነ» ብሎ የሚያስብ ከሆነ፣ እነዚ ሰዎች ከዚህ በኋላ ከኃጢያት ነጻ ሊሆኑ ይችላሉን? ሁኔታው እንደዚህ አይሆንም።

ምህረት የሚደረግለት እሱ/እሷ የኃጢያት ክምር መሆናቸውን ያውቃሉ። እሱ/አሷም በትክክል ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጠመቅ የሰውን ልጆች ኃጢያትን በሙሉ እንደተቀበለና የነዚህንም ኃጢያት ፍርድ ለመክፈልም እንደሞተልን ያምናሉ ማለት ነው።

ምህረት ቢደረግልንም ባይደረግልንም፣ ሁላችንም በመደነባበር ከመኖር አናመልጥም። እኛ የኃጢያት ክምር ነን። እኛ የሆንነው እንደዚህ ነው። እኛ ልንድን የምንችለው ኢየሱስ ኃጢያታችንን በሙሉ እንዳስወገደልን ያመንን ጊዜ ነው።

## እግዚአብሔር ቅንጣት ታህል ኃጢያት ያለባቸውን ምህረት አላደረገላቸውም




«ጥቂት ኃጢያት» ያለባቸውን እንኳን እግዚአብሔር ምህረት አላደረገላቸውም። «እግዚአብሔር፣ እኔ የሰራሁት ትንሽ ኃጢያት ነው» ወደ ሚሉት ፊቱን እንኳን አያዞርም። እግዚአብሔር ርህራሄን የሚያሳየው «እግዚዘብሔር ሆይ! እኔ የኃጢያት ክምር ነኝ። ወደ ገሃነም እሳትም ልገባ ነው። እባክህ

አድነኝ» ለሚሉት ነው:: «እግዚአብሔር ሆይ! እኔ ልድን የምችለው አንተ ካዳንከኝ ብቻ ነው:: ለምህረት በተደጋጋሚ አልጸልይም፣ ምክንያቱም በኃጢያት ላይ ኃጢያት ከመጨመር ውጭ ምንም እንደማላመጣ አውቃለሁና:: እባክህ አድነኝ!» ሙሉ በሙሉ ኃጥኣንን የሆኑት የሚለምኑት እንደዚህ ነው::

እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ በርሱ የሚመኩትን ያድናል:: እኔም ራሴ በየቀኑ የምህረት ጸሎትን አደርግ ነበር፣ ሆኖም ግን የምህረት ጸሎት ከኃጢያት ሊያነጻኝ አልቻለም:: ስለዚህም በጉልበቴ ተንበርክኬ «እግዚአብሔር ሆይ! እባክህን ራራልኝ፣ ከኃጥያትም አንጻኝ አድነኝም» ብዬ ጸለይኩ:: እንደዚህ ብለው የሚጸልዩትም ይድናሉ:: እነርሱም በእግዚአብሔር ምህረትና በኢየሱስ ክርስቶስ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቁ አምነዋል:: እነርሱም ይድናሉ::

እግዚአብሔር የሚቀበለው ራሳቸውን የኃጢያት ክምርና ክፋት ሰሪዎች መሆናቸውን ያወቁትን ብቻ ነው:: «እኔ የሰራሁት ይህቺን ጥቂት ኃጢያ ነውና እባክህ ማረኝ» የሚሉት አሁንም ድረስ ኃጥኣን ስለሆኑ እግዚአብሔረ ሊያድናቸው አይችልም:: እግዚአብሔር የሚያድነው ራሳቸውን የኃጢያት ክምር መሆናቸውን የሚያምኑትን ብቻ ነው::

በኢሳያስ 59:1-2 ላይ እንደተጻፈውም:- *«እነሆ የእግዚአብሔር እጅም ከማዳን አላቋረጠችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቆረችም፣ ነገር ግን በደላችሁ በእናንተና በአምላካችሁ መካከል ለይታለች፣ እንዳይሰማም ኃጢያታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል::»*

የኃጢያት ክምር ሆነን ስለተወለድን፣ እግዚአብሔር በትኩረት አይመለከተንም:: ይህ የሆነው እጁ አጥሮ አይደለም፣ ጆሮውን ከብዶታል፣ ለይቅርታው ብንለምነውም አይሰማንም::

እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ይነግረናል:- «በደላችሁ እኔን ከእናንተ ለይቶናል፣ በደላችሁም በእናንተና በእኔ መካከል ፊታችንን ለይታለች፣ ስለዚህም አልሰማችሁም::» በልባችን ውስጥ ብዙ ኃጢያት ስላለብንም፣ ገነት ለመግባት አንችልም፣ በሮቹ ምንም ያህል በስፋት ቢከፈቱም::

እኛ፣ በየጊዜው ኃጢያት የምንሰራ ሰዎች፣ ኃጢያ በሰራን ቁጥር ይቅርታ ይደረግልን ዘንድ የምንለምን ከሆነ፣ እግዚአብሔር ልጁን በተደጋጋሚ መግደል ይኖርበታል::

እግዚአብሔርም ይህን ለማድረግ አይፈልግም:: እንዲህም ይላል «ከነኃጢያታችሁ ወደ እኔ አትምጡ:: ከኃጢያታችሁ ሁሉ እንዲያነጻችሁ አንድ ልጄን ልኬኣለሁ:: ሁላችሁም እርሱ ኃጢያታችሁን እንደወሰደና ይህንንም እውነት መቀበል አለባችሁ:: በመቀጠልም፣ በውኃና በመንፈስ ወንጌል በማመን ዳኑ:: ይህ፣ ለናንተ ለፍጥረቶቼ የሰጠዋችሁ ታላቁ ፍቅር ነው::»

እግዚአብሔር የሚነግረን ይህንን ነው:: «በልጄ እመኑና ለኃጢያታችሁ ምህረትን ታገኛላችሁ:: እኔ፣ የእናንተ እግዚዘብሔር አንድ ልጄን ወደ እናንተ የላኩት ከኃጢያትና ከበደሎቻችሁ እንዲያድናችሁ ነው:: በልጄ አምናችሁ ዳኑ::»

የኃጢያት ክምር መሆናቸውን የማያውቁና በየእለቱ ለሚሰሩት ኃጢያት ይቅርታን የሚለምኑ ሰዎች አሉ:: ምን ያህል ክብደት ያለው ኃጢያት እንደተሸከሙ እንኳን ሳያውቁት፣ በፊቱ ተንበርክከው «እባክህን ለሰራኋት ትንሽ ኃጢያት ይቅርታን አድርግልኝ:: ይህንንም ደግሜ አላደርገውም» በማለት ይጸልያሉ::

አነዚህም በእንደዚህ አይነት ጸሎቶች እሱንም ሊያታልሉት ይፈልጋሉ:: እኛ ኃጢያትን የምነሰራው አንድ ግዜ ብቻ ሳይሆን እስክንሞት ድረስ ያለማቋረጥ ነው:: ስለዚህም በእያንዳንዱ ቀን እስከምንሞትበት ቀን ድረስ በየእለቱ ስለሰራነው ኃጢያት መጸለይ ይኖርብናል፣ ስጋችንም የኃጢያት መገልገያ ስለሆነ ኃጢያት መስራትን አናቆምም::

በየቀኑም በጣም ብዙ አይነት ኃጢያቶችን ስለምንሰራ፣ የአንድ ነጠላ ኃጢያ ይቅር መባል፣ ያለንን ችግር አይፈታውም:: ስለዚህም፣ ከኃጢያት ነጻ ልንሆን የምንችልበት ብቸኛ መንገድ ያለብንን ኃጢያት በሙሉ ወደ ኢየሱስ በማስተላለፍ ነው::



መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጆችን ኃጢያት ከዚህ በሚከተለው ሁኔታ ያብራራል:- *«እጃችሁ በደም፣ ጣታችሁም በበደል ረክሳለች፣ ከንፈራችሁም ኃጢያትን ተናግሯል፣ ማላሳችሁም ኃጢያትን አሰምቷል:: በጽድቅም የሚጠራ በእውነትም የሚፈርድ የለም፣ በምናምንቴ ነገር ታምነዋል ሃሰትንም ተናግረዋል፣ ጉዳትን ጸንሰዋል በደልንም ወልደዋል:: የእባብን እንቁላል ቀፈቀፉ፣ የሸረሪትንም ድር አደሩ፣ እንቁላላቸውንም የሚበላ ሰው ይሞታል፣ እንቁላሉም ሲሰበር እፉኝት ይወጣል:: ድሮቻቸውም ልብስ አይሆኑላቸውም፣ በስራቸውም አይሸፈኑም፣ ስራቸውም የበደል ሥራ ነው፣ የግፍም ሥራ በእጃቸው ነው:: እግሮቻቸው ወደ ክፋት ይሮጣሉ፣ የንጹሐውን ደም ለማፍሰስ ይፈጥናሉ፣ አሳባቸው የኃጢያት ኣሳብ ነው:: ጉስቁልናና ቅጥቃጤ በመንገዳቸው አለ:: የሰላምን መንገድ አያውቁም፣ በአካሄዳቸውም ፍርድ የለም:: መንገዳቸውንም አጣመዋል፣ የሚሄድባትም ሁሉ ሰላምን አያውቅም:: (ኢሳያስ 59:3-8)*

የሰው ልጆች እጆች በበደል ተጨማልቀዋል፣ በህይወት ዘመናቸውም ሊሰሩ የሚችሉት ኃጢያትን ብቻ ነው:: የሚሰሩት ነገርም ሁሉ ክፋት ነው:: እንዲሁም ምላሶቻችንም *«ውሸትን ተናግረዋል»*:: ከአፋችን የሚወጡት ነገሮች በሙሉም ውሸት ናቸው::

*«ዲያብሎስ ሃሰትን ሲናገር፣ ከራሱ ይናገራል፣» (ዮሐንስ 8:44)* «እውነት እየነገርኳችሁ ነው....... አሁንም እውነትን እነግራችኋለሁ:: የምላችሁ እውነት ነውም......» ቢሉ እንደገና ያልተወለዱት፣ የሚያወሩት ሁሉ ውሸት ነው:: ይህ እንደተጻፈው ነው:: «ዲያብሎስ ሐሰትን ሲናገር፣ ከራሱ ይናገራል::»

ሰዎች እምነታቸውን በባዶ ቃላት ላይ በማድረግ ውሸትን ይናገራሉ:: ሰዎች ክፋትንም በመስራት የበለጠ በደልን ይጨምራሉ:: የእባብን እንቁላል ያስታቅፋሉ፣ የሸረሪትንም ድር ያደራሉ:: እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- *«እንቁላላቸውን የሚበላ ይሞታል፣ እንቁላላቸውም ሲሰበር እፉኝት ይወጣል::»* እግዚአብሔር በልባችሁ ውስጥ የእባብ እንቁላል እንዳለ ይናገራል:: የእባብ እንቁላል! በልባችሁ ውስጥ ክፋት አለ:: በውኃውና በደሙ ወንጌል አምነን ምህረትን ማግኘት ያለብንም ለዚህ ነው::

ስለ እግዚአብሔር ለማስተማር በጀምረኩበት ቦታ ሁሉ «ኦ ወዳጄ! እባክህን ስለ እግዚአብሔረ አታንሳብኝ፡፡ ሁል ጊዜ አንድ ነገር ለመስራት ሳስብ ኃጢያት ከውስጤ ይወጣል፡፡ ልክ እንደሚፈስ ጎርፍ ይወርዳል፡፡ አንድ እርምጃ እንኳን ኃጥያትን ሳላደርግ መራመድ አልችልም፡፡ እኔም ምንም ማድረግ አልቻልኩም፡፡ በኃጢያትም የተሞላሁ ነኝ፡፡ በቃ ባጠቃላይ ተስፋ ቆርጫለሁ፡፡ እና እባክህን ጭራሽ ለኔ ስለ ቅዱሱ እግዚአብሔር አታንሳብኝ» አለኝ፡፡

ይህ ሰው የኃጢያት ክምር መሆኑን ያውቃል፣ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ከኃጢያቱ ሙሉ በሙሉ በፍቅሩ ወንጌል እንዳዳነው ግን አያውቅም፡፡ ራሳቸውን የኃጢያት ክምር እንደሆኑ የሚያውቁ ብቻ ይድናሉ፡፡

በእርግጥም ሁሉም እንደዚህ ነው፡፡ ሁሉም ሰው በሚሄድበት ቦታ ሁሉ ኃጢያትን ያደርጋል፡፡ ኃጢያት ዝም ብሎ ይፈሳል፣ ምክንያቱም ሁሉም ሰው የኃጢያት ክምር ነውና፡፡ ከእንደዚህ አይነት ህይወት ልንድን የምንችለው በእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው፡፡ በቀላሉ የሚገርም አይደለምን? ሲናደዱም፣ ሲደሰቱም፣ እንዲሁም ሲመቻቸውም ጭምር ኃጢያትን የሚሰሩ ሁሉ ሊድኑ የሚችሉት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ኢየሱስ የመጣው ሊያድነን ነው፡፡

እርሱም የሁላችንንም ኃጢያት አውጥቶልናል፡፡ የኃጢያት ክምር መሆናሁን እመኑና ዳኑ፡፡✉